# የአካባቢ ልማት ለዘላቂ እፎይታ

ኢብሳ ነመራ

ከሰባት አስርት ዓመታት በፊት የኢትዮጵያ መሬት 40 ከመቶ ገደማ በደን የተሸፈነ እንደነበረ መረጃዎች ያመለክታሉ። የዛሬ አርባ ዓመት ግን ይህ ሽፋን ከ10 በመቶ በታች ወረደ። በ70ዎቹ መጀመሪያ ላይ ደግሞ 4 በመቶ ያህል ብቻ ነበር። በየአካባቢው ካሉ አዛውንቶች የሚገኙ መረጃዎችም የዚህን 40 በመቶ የነበረው ደን በዚህ ደረጃ የማሽቆልቆሉን ትክክለኝነት" ያመለክታሉ። በአርባዎቹና በሃምሳዎቹ እድሜ ክልል ያለነው ኢትዮጵያውያንም ቢሆን፤ በተለይ ገጠር ያደግነው በእጽዋት ተሸፍኖ የነበረው መሬት እጅግ መሳሳቱን መመስከር እንችላለን።

እኔ በግሌ ከሰላሳ አምስት ዓመታት በፊት ልጅነቴን ያሳለፈኩበትን የማወቀውን አካባቢ ከሁለት ዓመት በፊት የማየት አጋጣሚ አግኝቼ ያየሁትን ለማመን ተቸግሬያለሁ። በእንጆሪ፣ በአጋምና በመሰል ተክሎች ተሸፍኖ የነበረውና ከብቶች የሚሰማሩበት ሰፊ መሬት የድሮውን ምልክቱን አንድም ሳይተው የእርሻ ማሳ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። በቁጥቋጦው ይጠለሉ የነበሩትን የተለያየ ዝርያ ያላቸው ጥንቸሎችና መሰል አነስተኛ እንስሳት አሁን በአካባቢው የሚኖሩ ህጻናት አያውቋቸውም። ወደመንደር እየዘለቁ፤ አንዳንዴም በሰብል ላይ ጉዳት ያደርሱ የነበሩ ከርከሮዎች አሁን የሉም። በበጋ ለአካባቢው እንግዳ የሆነ ሰው መልካ ተፈልጎለት ልብሱን ሰብስቦ ይሻገረው የነበረው ወንዝ ህጻናት ዘልለው የሚሻገሩት ትንሽ ጅረት ሆኗል። እርግጥ፤ በዚህ ጊዜ ውስጥ የአካባቢው ህዝብ ቁጥር በሶስት እጥፍ ገደማ አድጓል። ድሮ በቁጥቋጦ ተሸፈኖ የነበረው ቦታ አሁን የእርሻ ማሳ ሆኗል። ይህን መሬት ወደእርሻ ማሳነት የቀየረው አዲሱ ትውልድ ነው።

ይህ የእኔ ተሞክሮ በሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች ያለውን እውነታ ያንጸባርቃል። በ2003 ዓ.ም በተለይ በአማራ ክልል ደቡብ ወሎ ዞን፤ እንዲሁም በትግራይ ክልል የተለያዩ ዞኖች የተሰሩ የተፈጠሮ ሃብት እንክብካቤና የተፋሰስ ልማት ስራዎችን የመጎብኘት እድል አግኝቼ ነበር። በዚህ ጉብኝት የታዘብኩት ነገር ይህን የሚያረጋግጥ ነው። በእነዚህ የአማራና የትግራይ አካባቢዎች የተፈጥሮ ሃብት ላይ የደረሰው ውድመት ረዘም ያለ እድሜ ያስቆጠረ ነው። እድሜያቸው በአርባዎቹ ክልል ያሉ ሰዎች እነኳን ስለአካባቢው የቀድሞ ገጽታ  የሚያውቁት ነገር ምንም የለም። አዛውንቶች ናቸው ትውስታ ያላቸው፤ በተፈጥሮ አካባቢዎቹ ላይ ጉዳት መድረስ ከጀመረ ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ አስቆጥሯል። የአካባቢዎቹን የቀድሞ ገጽታ የሚያመለክቱ ማስረጃዎች ግን አሁንም አሉ። ዋነኞቹ የቤተክርስቲያን ግቢዎች ናቸው። የደከመው ሰው ቀትር ላይ የሚያርፍበት ዛፍ በሌለበት ምድረ በዳ የሚገኙ የቤተክርስቲያን ግቢዎችና ገዳማት ተለየተው አረንጓዴ ደሴት ሆነው ይታያሉ። እነዚህ የቤተክርስቲያን አጸዶች ድሮ አካባቢው በዛፍ የተሸፈነ እንደነበረ ብቻ አይደለም የሚመሰክሩት፤ በአካባቢው የነበሩት አገር በቀል ዛፎች ምን አይነት እንደነበሩም ያሳያሉ።

ከላይ በአጭሩ ያነሳሁት እውነታ የተፈጥሮ አካባቢያችን ላይ ምን ያህል ጉዳት እንደደረሰ ሁላችንም የየራሳችንን አካባቢ በማስታወስ እንድንገነዘብ ለመኮርኮር ያህል ነው። ይህ በተፈጥሮ ላይ የደረሰው ጉዳት አሁን በመንግስትና በህዝብ ልዩ ተኩረት ተሰጥቶታል። የወደመው ተፈጥሯዊ አካባቢ እንዲያገግም የተቀናጀ የአካባቢ ልማት/የተፋሰስ ልማት ስራ እየተከናወነ ይገኛል። በተለይ ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ ትልቅ ለውጥ ያመጣ የአካባቢ ልማትና እንክብካቤ ስራ ተከናውኗል። እነዚህ የአካባቢ ልማቶች እስከ 50 በመቶ ተዳፋት በሆኑ የተራቆቱ ተራራዎችና ኮረብታዎች ላይ እርከን በመስራት፣ ዛፍና ሳር በመትከል ላይ ያተኮረ ነው። ከዚህ በተጨማሪ፤ በራሳቸው ሊያገግሙ የሚችሉ አካባቢዎችን ከሰውና ከእንስሳት ንክኪ በመከላለል ድንቅ ውጤት ተገኝቷል።

በዚህ ዙሪያ የተከናወኑና ሊከናወኑ በታቀዱ ተግባራት ላይ መረጃዎችን ከማቅረቤ በፊት በትግራይ ክልል አሁን መጠሪያውን በማላስታውሰው አካባቢ ከአርሶ አደሮች የሰማሁትን አንድ ነገር ላካፍላችሁ ወድጃለሁ። የአካባቢው የተፈጥሮ ሃብት ክፉኛ የተጎዳ እንደነበረ ሰምቻለሁ። በአካባቢው የሚገኝ ተራራ ያገጠጠ ድንጋይ እንደነበረ፣ በአካባቢው ፊጪጭ የሚል ውሃ እንዳልነበረ አርሶ አደሮቹ አጫውተወኛል። እኔ በተመለከትኩበት ወቅት ግን ከጉዳቱ ይልቅ በማገገም ላይ ያለ መሆኑ ነው ጎልቶ የሚታየው። በተራራው ላይ የተለያዩ የተፋሰስ እንክብካቤ ስትራክቸሮች ተገንብተዋል። የድንጋይ እርከኖች፤ የተለያየ ቅርጽ፣ ስፋትና ጥልቀት ያላቸው የውሃ መከተሪያ ጉድጓዶች ወዘተ. በተራራው ላይ ይታያሉ። ጋራው በሰምበሌጥ ሳር ተሸፍኗል። ቁጥቋጦዎች ወርሰውታል። ገና እድገታቸውን የጀመሩ የተለያየ ዝርያ ያላቸው ዛፎች እዚህም እዚያም ይታያሉ።

ይህ ብቻ አየደለም፤ የአካባቢው ሰዎች አይተዋቸው የማያውቋቸው ምንጮች ከተራራው ስር ኩልል ያለ ውሃ ያፈስሳሉ። ከተራራው ስር መንጭተው የሚፈሱት ወንዞች ሰፊ ጉድጓድ ተቆፈሮላቸው ተገድበዋል። ወቅቱ በጋ ቢሆንም ምንጩ የሚፈስስበት አካባቢ ለምለም አረንጋዴ ነው። ምንጮቹ የተገደቡበት አካባቢ በመስኖ የለሙ የበቆሎና የተለያዩ የአትክልት ማሳዎች ይታያሉ። ከብቶች ከየአካባቢው መጥተው ከተከተረው ሰፊ ጉድጓድ ውሃ ይጠጣሉ። የአካባቢው ነዋሪዎች ድሮ አንድ ዘለላ ነዶ የማይታይበት ጋራ ያበቀለውን ከሰው ቁመት የሚረዝም ሳር እያጨዱ ከብቶቻቸውን ይመግባሉ።

ታዲያ ይህን በጉልህ የሚታይ ለውጥ ያመጣ ስራ ለማከናወን ምን እንዳነሳሳቸው የአካባቢውን አርሶ አደሮች ጠየኳቸው። ሳይዋሹ ነገሩኝ። እኛ በራሳችን አልተነሳሳንም ነበር ያሉኝ፤ ወደአንድ ወጣት የግብርና ባለሞያ እያመለከቱኝ፤ እርሱ ነው ዘውትር እየመጣ እየሰበሰበ፣ እያስተማረ፣ እየመከረ ለስራ እንድንወጣ ያደረገን አሉኝ። ታዲያ መጀመሪያ ባለሞያውን ጠላነው። መጥላት ብቻ አይደለም፤ ረግመነዋልም። እየረገምነው የጀመርነው ስራ አሁን ውጤት አስገኝቷል። እናም የስራችንን ውጤት ማየት ስንጀምር፣ ባለማወቃችን

ባደረግነው ተጸጽተን ባለሞያውን መልሰን መረቅነው። አሁን እየመረቅነው ነው አሉኝ። እርግማንን ወደ ምርቃት የለወጠ ድንቅ ተግባር፣ ድንቅ ወጤት!

በዚህ በጠቀስኩት አካባቢ የተገኘው ውጤት ባለፉት አስር ዓመታት በበርካታ የአገሪቱ አካባቢዎች የታየ ነው። በአካበቢ ልማትና እንክብካቤ የተከናወነው ተግባር በየአካባቢው የውሃ ምንጮችን አስገኝቷል። ደርቀው የነበሩ ጅረቶች ዓመቱን ሙሉ እንዲፈሱ፣ መጠናቸው ቀንሶ የነበሩ ወንዞች እንዲጨምር አድርጓል። በየአካባቢው አነስተኛ የመስኖ እርሻ ማከናወን ተችሏል። የመጠጥ ውሃ፤ የከብቶች መኖና ውሃ በቅርብ ማግኘት አስችሏል። በብዙ አካባቢዎች ባለፈው ዓመት ተከስቶ የነበረውን ድርቅ በመጠኑ መከላከል የሚያስችል አቅም ለመፍጠር ማገዙንም መረጃዎች ያመለክታሉ። ምንም ጥቅም የማይሰጡ የነበሩ ተዳፋት አካባቢዎች መልማታቸው ለገጠር ስራ አጥ ወጣቶች የስራ እድል የፈጠረ ተጨማሪ ሊለማ የሚችል መሬት አስገኝቷል። በርካታ ወጣቶች ተደራጅተው በተዳፋት አካባቢ የበቀለን ሳር ለከብት መኖነት በመጠቀም የከብት ማደለብና ርባታ ስራ ላይ መሰማራት ችለዋል። ወደለምነት የተቀየረው አካባቢ በርካታ ወጣቶችን በማር ልማት ስራ ላይ ማሰማራት አስቿሏቸዋል።

የተፋሰስ ልማት ስራ ዘላቂ ፋይዳም አለው። በየአካባቢው ለተለያየ ዓላማ የሚገነቡ ግድቦችን፤ በተለይ ታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ከደለል በመከላከል የተገነቡበትን ዓላማ በአግባቡ ማከናወን እንዲያስችሉ፤ የፕሮጀክት እድሜያቸውን ሙሉ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ ያስችላሉ። በተለይ ከታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ መጀመረ በኋላ በአባይ ተፋሰስ ውስጥ የሚገኙ አርሶ አደሮች የሚያከናውኑት የተፋሰስ ልማት ግድቡን ከደለል የመከላከል ግብ ያለው መሆኑን ማወቃቸው ከፍተኛ ተነሳሽነት እንደፈጠረባቸው ይታወቃል። ይህ ተግባራቸው ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ እንዳበረከቱት አስተዋጽኦም ተቆጥሮላቸዋል።

ያም ሆነ ይህ፤ የተፋሰስ ልማትና የአካባቢ እንክብካቤ ስራ አሁንም ቀጥሏል። በያዝነው ወር በአምስት ክልሎች (በትግራይ፤ በአማራ፤ በኦሮሚያ፤ በደቡብ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች፤ በቤኒሻንጉል ጉምዝ ) የ2009 ዓ.ም የተፈጥሮ ሃብት ልማት ስራ በይፋ ተጀምሯል። በዘንድሮው የተፈጥሮ ሃብት ልማት ስራ ላይ ከ24 ሚሊዮን በላይ ዜጎች ይሳተፋሉ ተብሎ ይጠበቃል። በዝግጅት ምእራፉ በእነዚህ ክልሎች ለሚከናወነው የተፈጥሮ ሃብት ልማትና ጥበቃ ስራ 6 ሺህ 706 ተፋሰሶችን ለማልማት መታቀዱን የእርሻና የተፈጥሮ ሃብት ሚኒስቴር አስታውቋል። ከ15 ሚሊዮን በላይ ለስራው የሚያስፈልጉ የእጅ መሳሪያዎችም መዘጋጀታቸውን፣ ከ2 ነጥብ 2 ሚሊዮን በላይ አርሶ አደሮችና ባለሙያዎች፤ እንዲሁም ቀያሽ አርሶ አደሮች በተፋሰስ ልማት ዙሪያ አስፈላጊውን ስልጠና እንዲያገኙ መደረጋቸውንም ሚኒስቴሩ ገልጿል።

የተፈጥሮ ሃብት ልማትና እንክብካቤ ስራው ዓላማ ባለፉት አስር ዓመታት ሲከናወን እንደነበረው ሁሉ፣ በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ ምክንያት የተጎዳ መሬት እንዲያገግም በማድረግ መሬቱ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ማሳደግ ነው። የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ ስራው የተራቆተውን መሬት ከንክኪ ነፃ ማድረግ፣ እርከን መስራት እና እፅዋት በመትከል በስነ ህይወታዊ መንገድ የተራቆተ መሬት መልሶ እንዲያገግም ማስቻልን ያጠቃልላል።

የዘንድሮውን የተፈጥሮ ሃብት ልማት ስራ መጀመር አስመልክቶ የእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ሚኒስትር ዲኤታው ዶክተር ካባ ኡርጌሳ በሰጡት መግለጫ፣ በአገር አቀፍ ደረጃ እየተከናወነ ያለው የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ስራ በርካቶችን ተጠቃሚ ማድረጉን አስታውቀዋል። በተመሳሳይ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአካባቢ ጥበቃና ልማት ተመራማሪ የሆኑት ዶክተር በላይ ስማኔ፣ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ስራው አገሪቱ የተሻለ እንድትለማ የሚደደርግና ተጠናክሮ ሊቀጥል የሚገባው ነው፣ በየጊዜው የሚካሄደው የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ ልማት ይበልጥ ተጠናክሮ እንዲጓዝ እና አርሶ አደሩን ተጠቃሚ እንዲያደርግ ማህበረሰብ አቀፉ ስራ በሳይንስና በምርምር መታገዝ አለበት ብለዋል። የእርሻ እና ተፈጥሮ ሃብት ሚኒስቴርም በየዓመቱ የሚካሄደውን የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ በሳይንሳዊ ቅኝት አርሶ አደሩን ይበልጥ ተጠቃሚ በሚያደርግ ስልት እንደሚሰራ አስታውቋል።

እንግዲህ በያዝነው ወር መጀመሪያ ላይ በይፋ የታወጀው የዘንድሮው የተፈጥሮ ሃብት ልማት ስራ በተለይ በአማራና በኦሮሚያ ክልሎች ወደተግባር መሸጋገሩን የእርሻና የተፈጥሮ ሃብት ሚኒስቴር አስታውቋል። ሌሎቹም ክልሎች የሰብል ምርት ተሰብስቦ መጠናቀቁን ተከትሎ እንቅስቃሴ ይጀምራሉ ተብሎ ይጠበቃል።

በእንግዲህ የአገራችን የተፈጥሮ ሃብት ባለፉት ሰባት አስርት ዓመታት ከፉኛ መጎዳቱ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ያስማማል። ጉዳቱ ለሰዉም ተርፏል። የአየር ንብረት መዛባት - ድርቅ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየበረታ ሄዷል። በተፈጥሮ ሃብት መጎዳት ምንጮች፣ ጅረቶችና ወንዞች በመድረቃቸው የህዝቡ በተለይ የአርሶና አርብቶ አደሩ የድርቅን ተጽእኖ የመቋቋም አቅሙ እጅጉን የተዳከመበት ሁኔታ ተስተውሏል። ድሮ ወረድ ተብሎ ይቀዳ የነበረ ውሃ አሁን ሙሉ ቀን መጓዝን እየጠየቀ የመጣባቸው አካባቢዎች አሉ። እነዚህን ተጽእኖዎች ለማስቀረት ብቸኛው አማራጭ የተፈጥሮ አካባቢን ማልማት፣ የለማውንና ከውድመት የተረፈውንም መንከባከብ ነው።

ባለፉት አስር ዓመታት በየዓመቱ በሃያ ሚሊዮን የሚቆጠሩ አርሶ አደሮች ለበርካታ ቀናት በተፈጥሮ አካባቢ ልማትና እንክብካከቤ ስራ ላይ ተሰማርተዋል። አሁንም ይህንኑ በማከናወን ላይ ናቸው። ይህ ስራ ነጭ ላብ ጠብ እስኪል የሚከናወን አድካሚ መሆኑ ይታወቃል። ከተገኘው ውጤት አኳያ ሲታይ ግን ዘላቂ እፎይታ የሚያስገኝ ነው። ይህ የተፈጥሮ አካባቢ ልማት ስራ የተጣለበት አርሶ አደር ስራው

አድካሚ ቢሆንም ዘላቂ እፎይታ የሚሰጥ መሆኑንና የወጤቱ ቀዳሚ ተጠቃሚም ራሱ መሆኑን ተገንዝቦ በወኔ ሊያከናውነው መነሳት አለበት። ሌሎች ባለድርሻ አካላትም ሳይልፈሰፈሱ ከአርሶ አደሩ ጎን መቆም አለባቸው። ለዘላቂ እፎይታ ዛሬን እንድከም!